# ቅዱሳን

ቅዱሳን የሚለው ቃል በግዕዝ ንጹሕ ልዩ መሆንን የሚያመለክት ነው። ይህ ቃል ለእግዚአብሔር የባሕርይ መግለጫ ነው። እግዚአብሔር በባሕርዩ ቅዱስ ነውና ቅድሳን የሚለውንም ቃል በባሕርዩ ቅዱስ የሆነውን አምላክ ሊያገለግሉ መላዕክትና ደጋግ ሰዎች የሚሰጥ ነው።

መላክትን ቅዱሳን እንላቸዋለን ከማንኛውም ክፉ ነገር የራቁ ሥርዓታቸውን የጠበቁ እግዚአብሔርን ያወቁ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ስለሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ። ከመዓረግ መላእክት የደረሱ ደጋግ ሰዎችም በዚሁ የቅድስና ስም ይጠራሉ። ራሱ እግዚአብሔር "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ዘሌዋ 19፡2 1ጴጥ 1፡15-16

ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት ሁሉ ለቅዱስ እግዚአብሄር ሲሉ ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገው ስለሰጡ፣ ለስሙ ስለ መሰከሩ፣ በተጋሉአቸውና በትሩፋታቸው ስላገለገሉ የቅድስናና የብፅዕና ማዕረግ ተሰጥቶአቸዋል፣ ይሰጣቸዋልም ጌታችንም በወንጌል "አባት ሆይ በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ ቅዱስ ነው" ብሎ ስለቅድስናቸው ተናግሮአል። ዮሐ 17፡17

## 4.1 ቅዱሳን በገድል በሶስት ይከፍላሉ

1. በአላውያን (በማያምኑ) ነገሥታት ፊት ስለ ክርስቶስ አምላክነት ሣያፍሩ፣ ሣይፈሩ መስክረው እስከ ደም ጠብታ ድረስ ለክርስቶስ የመሰከሩ ሰማዕታት ናቸው። ሰማዕት ማለት መስካሪዎች ማለት ነው።

በዲያቆን ኢሐዱ አስረስ፡-

ባላለን፣ ኢሳያስም የዘላለም መታሰቢያ ስም እሰጣቸዋለሁ ብሎ እግዚአብሔር መናገሩን ባልፃፈልን ነበር። ከላይ የተመለከትነው መታሰቢያ ስም እንዳላቸው እንጂ የቅዱሳን መታሰቢ የሚረሳ አለመሆኑን ነው። ኃጥአን ግን መታሰቢያ የላቸውም ተረስቷል። ቅዱሳን እንኳን መታሰቢያ ላይኖራቸው ቀረቶ ከማማለድም አልፎ እስከ መፍረድ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል። ማቴ 19፡28

ይህን ላልተረዱ የልድያን ልብ ከፈቶ ያስረዳ አምላክ ይህን ድንቅ እውነት ያስረዳልን ሐዋ 16፤15-16

www.ethiopianorthodox.org